# ድህነትን ታሪክ ለማድረግ የተቀናጀ ዘመቻ

# (ክፍል ሁለት)

**ተስፋዬ ለማ**

በክፍል አንድ በአገራችን በመስፋፋትና በመገንባት ላይ ያሉ ነባርና አዳዲስ የስኳር ልማት ፕሮጀክቶች ኢትዮጵያ የሚትመራበትን የግብርና መር ኢኮኖሚ ወደ እንዱስትሪ መር ኢኮኖሚ ለማሸጋገር የሚያስችል መሰረት ለመጣል ከተያዙት ታላላቅ የእንዱስትሪ ልማቶች መካከል በዋናነት የሚጠቀሱ መሆኑን ዳሰናል። በአምስት ዓመቱ የእድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ መሰረት ነባሮቹን የማስፋፋትና አዳዲሶች የመገንባት አቅጣጫ ተይዞ እየተሰራ መሆነን ለማየት ተሞክሯል።

ከዚሁ ጋር ተያይዞም የአገሪቱ የስኳር ፍላጎት ከሚመረተው ምርት ጋር ባለመጣጣሙ መንግስት ከተለያዩ አገራት በከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ ስኳር እያስገባ መሆኑን ጠቁመን ከሶስት ዓመታት በኋላ ግን አገሪቱ የህዝቧን የስኳር ፍላጎት አሟልታ የተረፈውን ለውጭ ገበያ በማቅረብ የውጭ ምንዛሪ የሚታስገባበት ሁኔታ እንደሚፈጠር አይተናል።

ከስኳር ልማት ፕሮጀክቶቹ ጋር ተያይዞ በተለያዩ ወገኖች የሚነሱ መሰረትየለሽ አሉታዊ ዘገባዎች የአገራችንን የልማት አቅጣጫ ለማስቀየስ እንጂ መሰረታዊ ጠቀሜታ ኖሯቸው እንዳልሆነና በአሁኑ ወቅት ልማታችንን ለማደናቀፍ የሚሰነዘሩ አሉቧልታዎችን የሚሰማ ጆሮ ያለው ኢትዮጵያዊ አለመኖሩንም ለማስገንዘብ ተሞክሯል። የኢትዮጵያ ህዝብ ዋናው ጠላቱ ድህነት መሆኑን መግባባት ላይ መደረሱን ቃኝተናል።

በመሆኑም የኢትዮጵያ ህዝብ እነዚህ አሉቧልታዎች እንደማይበግሩት በመጥቀስ በእያንዳንዱ የስኳር ልማት ፕሮጀክት ያለው የአፈጻጸም ሁኔታና በአጠቃላይ ለኢትዮጵያ ህዝብ በተለይ ደግሞ ለአካባቢው ነዋሪዎች ሊያስገኝ የሚችለው ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታ በሚመለከት በቀጣይ ክፍሎች እንደምናቀርብ መግለጻችን ይታወሳል።

በዚህ መሰረት በሁለት ክፍለን ለማየት እንሞክራለን። በመጀመሪያ በመገንባት ላይ ያሉ አዳዲሶቹን ቀጥለን ደግሞ የማስፋፊያ ስራ እየተሰራባቸው ያሉ ነባር የስኳር ፋብሪካዎችን እናያለን። በአሁኑ ወቅት እየተገነቡ ካሉት አዳዲስ የስኳር ልማት ፕሮጀክቶች መካከል የወልቃይት ስኳር ልማት ፕሮጀክትን በዚህ ክፍል እንመለከታለን።

የወልቃይት የስኳር ልማት ፕሮጀክት ከ8 ቢሊየን ብር በላይ በሆነ ወጪ የሚገነባ ነው። አካባቢው ለሸንኮራ አገዳ ተስማሚ መሆኑ በጥናት በመረጋገጡ በአገሪቱ የተለያዩ አካባቢዎች ለመገንባት ከታቀዱት አስር አዳዲስ የስኳር ፋብሪካዎች አንዱ በወልቃይት እንዲሆን በመደረጉ ከግድቡ ጋር ተያያዥነት ያላቸው መሰረተ ልማቶች እየተገነቡ ሲሆን በተለይም የፕሮጀክቱ አካል የሆነው የሜይዴይ ግድብ ግንባታ

በመከናወን ላይ ይገኛል። ከአካባቢው የተገኘ መረጃ እንደሚያሳየው እስካሁን ባለው ሁኔታ 10 በመቶ የሚሆነው ሥራ ተከናውኗል።

የሜይዴይ ግድብ የዛሬማ ወንዝን መሰረት አድርጎ በመገንባት ላይ ይገኛል። የግድቡ አፈር ቁፋሮ ስራ ከ90 በመቶ በላይ የተጠናቀቀ ሲሆን ከዚሁ ጎንለጎን ወንዙን የመጥለፉና የመቀየስ ሥራም ከ70 በመቶ በላይ መጠናቀቁን መረጃው ያሳያል።

የሜይዴይ ግድብ የሚያርፈው 36 ሄክታር መሬት ላይ ሲሆን በግድቡ ምክንያት በውሃ የሚሸፈነው መሬት ደግሞ 9 ሺሕ 6 መቶ 50 ሄክታር ነው። 1 መቶ 43 ሜትር ከፍታና 7 መቶ 20 ሜትር ርዝመት ይኖረዋል። የግድቡ ግንባታ ሙሉ በሙሉ ሲጠናቀቅ 3 ነጥብ 5 ቢሊዮን ክዩቢክ ውሃ የመያዝ አቅም እንደሚኖረው ይገመታል።

ይህ ግድብ በወልቃይት የስኳር ልማት ፕሮጀክት ከሚሰሩ ግድቦች ትልቁና ወሳኙ ግድብ ነው። ከዚሁ ጎንለጎን የቃሌማ ወንዝን መሰረት አድርጎ የሚሰራ የውሃ መቀልበሻ ውቅር አለ። መቀልበሻ ውቅሩ የሜይደይን ያህል ግዝፈት ባይኖረውም የጎላ ድርሻ እንደሚኖረው ግን ይታመናል። መቅልበሻ ውቅሩ 15 ሜትር ከፍታ ሲኖረው ግንባታው ሲጠናቀቅ 12 ሚሊየን ክዩቢክ ውሃ የማቆር አቅም ይኖረዋል ተብሎ ይታመናል። ይህ ግድብ ለእርሻ ልማት እንደሚውልና ከ3 ሺሕ 3 መቶ ሄክታር መሬት በላይ የማልማት አቅም እንዳለው ለማወቅ ተችሏል።

በአምስት ዓመቱ የእድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ በተቀመጠው አቅጣጫ መሰረት ባለፉት ሁለት ዓመታት በወልቃይት የስኳር ልማት ፕሮጀክት ለማከናወን በተያዘው ፕሮግራም መሰረት መፈጸሙ ከአካባቢው የተገኘ መረጃ ያሳያል። በሚቀሩት ሶስት ዓመታት ደግሞ አጠቃላይ የፕሮጀክቱ ግንባታ የሚጠናቀቅ ሲሆን ለአገሪቱ ኢኮኖሚ እድገት ከሚኖረው አስተዋጽኦ ባሻገር ለአካባቢው ነዋሪዎች ፈርጀ ብዙ ጠቀሜታ ይሰጣል። የአካባቢው ነዋሪዎች የሚናገሩትም ይሄንኑ ነው።

አቶ ታደለ ይልማ እና አቶ ተጠምቀ ገ/መድን ነዋሪነታቸው በወልቃይት ወረዳ ቃሌማ ገጠር ቀበሌ ገበሬ ማህበር ነው። ነዋሪዎቹ በአካባቢው እየተካሄደ ያለውን የስኳር ልማት ፕሮጀክት በሚመለከት ተጠይቀው እንደገለጹት ልማቱ ከመጀመሩ በፊት መንግስት ከህዝቡ ጋር ተከታታይ ውይይቶችን አድርጓል። ከተደረገው ውይይት በኋላ ሕብረተሰቡ ከልማቱ ተጠቃሚ እንደሚሆን መገንዘብ በመቻሉ ከመንግስት ጋር እጅና ጓንት ሆኖ በመስራት ላይ ይገኛል።

ልማቱ ለሌላው የኢትዮጵያ ህዝብ ከሚሰጠው ጠቀሜታ ባሻገር ለአካባቢው ሕብረተሰብ የሚሰጠው የተለየ ጥቅም ምንድን ነው? ከዚህ ልማት ጋር ተያይዞ እየተነሳ ያለው አሉቧልታ መሰረቱ ምንድን ንው? የህዝቡ ምላሽስ ምን ይመስላል? ለሚሉትን ጥያቄዎች ምላሽ መስጠት በልማቱ አጠቃላይ ገጽታ ላይ ግንዛቤ ለመያዝ ያግዛል።

የወልቃይት የስኳር ልማት ፋብሪካ ተጠናቆ ማምረት ሲጀምር አገሪቱ ያላትን የስኳር ፍላጎት ለማሟላት ያግዛል። ከተለያዩ አገራት ወደ አገር ውስጥ ለሚገባው ስኳር የምታወጣውን ከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ

ከማዳኑም ባሻገር አገሪቱ ለውጭ ገበያ ለማቅረብ ያቀደችውን የስኳር ምርት ለማሟላት የሚኖረው ድርሻ የጎላ ይሆናል። ይሁንና ለአካባቢው ነዋሪዎች የሚሰጠው ጠቀሜታ ደግሞ ከዚህም በላቀ ደረጃ ሊገለጽ ይችላል።

የአካባቢው ነዋሪዎች ከልማት ፕሮጀክቱ ከሚያገኙት ጥቅም አንዱ ሰፊ የስራ እድል ነው። የወልቃይት የስኳር ፕሮጀክት ከ46 ሺሕ በላይ ለሚደርሱ ዜጎች የስራ እድልን ይፈጥራል። እንደሚታወቀው ከስኳር ልማት ፕሮጀክቱ ጋር ተያያዥነት ያላቸው መሰረተ ልማቶችና የአገልግሎት ተቋማት ግንባታ ሥራዎችን የሚያካትት በመሆኑ ከቀን ሰራተኛ እስከ ከፍተኛ መሐንዲስ ድረስ የማሳተፍ አቅም ይኖረዋል።

በአገራችን ቀደም ሲል ተንሰራፍተው ከነበሩት ችግሮች መካከል አንዱ ሥራ አጥነት ነው። ሥራ አጥነትን ለመቅረፍ የተለያዩ ጥረቶች እየተደረጉ ባሉበት በአሁኑ ወቅት ይህንን ያህል የሰው ሃይል ሊያሰማራ የሚችል ፕሮጀክት በአካባቢው መገንባት ለነዋሪዎች የበለጠ ጠቀሜታ እንደሚኖረው የሚያጠራጥር አይደለም። በአገር ደረጃ የሥራ አጥነትን ችግር ከመቅረፍ አኳያ የሚኖረው ሚና በእጅጉ የጎላ ነው።

የወልቃይትና አካባቢው ህዝብ በሚፈጠረው የስራ ዕድሉ ይበልጥ ተጠቃሚ ይሆናል። ምናልባትም የማዕዱ ተቋዳሽ ይሆናሉ ተብሎ ከሚገመተው 50 ሺሕ መካከል አብዛኛዎቹ የአካባቢው ነዋሪዎች እንደሚሆኑ አያጠያይቅም። በየደረጃው በሚመጥናቸው የስራ መስክ በመሰማራት ህይወታቸውን ለመምራት አመች ሁኔታ ይፈጥርላቸዋል።

የአካባቢው ነዋሪዎች ከፕሮጀክቱ መመስረት ጋር በተያያዘ የሚያገኙት ሌላው ጥቅም ደግሞ መስኖ ገብ እርሻን ማልማት የሚያስችል ሁኔታ ስለሚፈጠርላቸው ነው። መስኖ ገብ ልማት በአገራችን ከቅርብ ዓመታት ወዲህ እየተለመደ የመጣና ምርትንና ምርታማነትን ለማሳደግ የሚያግዝ የግብርና ልማት አማራጭ ነው።

ቀደም ሲል በነበረው ኋላቀርና የዝናብን መምጣት እየተጠባበቁ የሚሰራ የእርሻ ልማት አንዳንዴ ጭራሹን በመጥፋት አንዳንዴ ደግሞ ከዓመት ጉርስና ልብስ የማያልፍ ምርትን በመቸር የህዝቡ ኑሮ ከእጅ ወዳፍ ብቻ እንዲሆን አስገዳጅ ሁኔታ የፈጠረበት ሁኔታ እንደነበር ይታወቃል።

ይሁንና ካለፉት 20 ዓመታት ወዲህ በተወሰነ ደረጃና በተወሰኑ የአገሪቱ ክፍሎች እየተለወጠና አርሶ አደሩ ውሃን የማቆር ተሞክሮ እየቀሰመ መምጣቱ ተስተውሏል። የወልቃይት የስኳር ልማት ፕሮጀክትም ይህንኑ ተሞክሮ በማጠናከር ነዋሪዎች በዓመት አንድ ጊዜ ብቻ ሳይሆን ሶስት ጊዜ የሚያመርቱበት ሁኔታ መፍጠር የሚያስችል እድል ይከፍታል።

ለሸንኮራ አገዳ ልማት የሚገደበው ግድብ የታቀደለትን ዓላማ ከመፈጸሙም ባሻገር በዙሪያው የሚገኙ አርሶ አደሮች የእርሻ ማሳ ጭምር እንዲያለማ ይደረጋል። በዚህ መልክ የአካባቢው አርሶ አደር የዝናብ ውሃ ላይ ጥገኛ ከመሆን ይገላገላል። ዝናብ በጠፋ ቁጥር ለርሃብ መዳረጉም አብሮ ያከትማል።

በዚህ መልክ የአካባቢውን አርሶ አደሮች ለዘመናት ለችግር ሲዳርግ የነበረው አንኳር ችግር ማቃለል ያስችላል። የምግብ እጥረቱን ከመፍታቱም በተጨመሪ የአርሶ አደሩን ምርትና ምርታማነት ለማሳደግ የጎላ

ድርሻ ይኖረዋል። የአካባቢው አርሶ አደሮች  እስካሁን  ከነበራቸው ኑሮ የተሻለ ኑሮ ለመኖር የሚያስችል ሁኔታ ይፈጠርላቸዋል።

የስኳር ልማት ፕሮጀክቱ ለአካባቢው ነዋሪዎች የሚኖረው ሌላው ጠቀሜታ እንስሳትን ለማርባትና ለማድለብ አመች ሁኔታ መፍጠሩ ነው። የፋብሪካውን ተረፈ ምርት በመጠቀም የአካባቢው ነዋሪዎች እንስሳትን በማርባትና በማድለብ በከፍተኛ ደረጃ ተጠቃሚ መሆን ይችላሉ።

የዓሳ ምርትን ማስፋፋት ደግሞ ሌላው ጠቃሚ ተግባር ይሆናል።  በአብዛኛው የአገራችን ክፍል ዓሳን አምርቶ መጠቀም የተለመደ አይደለም።  ይህ የሆነው ከሁለት መነሻ ነው። አንደኛው ሃይቆችና ትላልቅ ወንዞች ያሉባቸው አካባቢዎች ውስን በመሆናቸው ሲሆን ሌላው ደግሞ የግንዛቤ ችግር ነው። ሃይቆች ባሉባቸው አካባቢዎች ያለው የዓሳ ምርትም ቢሆን  አገሪቱ ማግኘት የሚገባት ያህል እንዳልሆነ ይታወቃል።

ይሁንና በወልቃይት የስኳር ልማት ፕሮጀክት በሚገነቡ ሰው ሰራሽ ሃይቆች ዓሳን በሰፊው ለማምረት የሚያስችል ሁኔታ ይፈጠራል። የአካባቢው ህዝብ ዓሳን ለምግብ አማራጭነት ከመጠቀም አልፎ ለገቢ ማስገኛ ሊጠቀሙበት የሚያስችል ሁኔታ ይኖራል።

በወልቃይት እየተካሄደ ያለ ልማት የዋልድባ ገዳምን የማይነካ ነው። የገዳሙ ማሕበረሰብም እንደሌላው የአካባቢው ህዝብ ተጠቃሚ ከመሆኑም ባሻገር በሚገነባው መሰረተ ልማት ምክንያት የገዳሙ ጎቢኚዎች ቁጥር እያደገ ስለሚመጣ ገቢውም በዚያ ልክ ስለሚጨምር መነኮሳቱ የበለጠ ተጠቃሚ ይሆናሉ።

ከዚህም በተጨማሪ የገዳሙ ማሕበረሰብ እስካሁን ድረስ የዓመት ዝናብን እየጠበቀ ያመርት የነበረው ሁኔታ ይቀርና በመስኖ በመጠቀም የእርሻ ምርቱን በዓመት እስከ ሶስት ጊዜ እንዲያመርት ያስችለዋል። ከዚህ አንጻር የዋልድባ ማሕበረሰብ ከልማቱ ተጠቃሚ እንጂ ተጎጂ እንደማይሆን መገመት አያስቸግርም።

እስካሁን ድረስ ባለው መረጃ መንግስት  በስኳር ልማት ፕሮጀክቱ 3 ሺሕ 4 መቶ 54 የሰራተኞች መኖሪያና 82 የአገልግሎት መስጫ የሚገነባ ሲሆን በስኳር ልማት ምክንያት ለሚነሱ ነዋሪዎች ደግሞ ከ5 ሺሕ በላይ ቤቶች ይገነባሉ።  የመንገድ፣ የመብራት፣ የስልክ እና የንፁህ  መጠጥ ውሃ አገልግሎቶችን ይዘረጋል። ትምህርት ቤቶችና ጤና ተቋማት ይገነባል።

በድምሩ  አስራ አንድ የገጠር መንደሮችና አንድ ከተማ እንደሚመሰረቱ  ከወልቃይት የስኳር ልማት ፕሮጀክት ጽሕፈት ቤት የሚገኙ መረጃዎች ይጠቁማሉ። በተጨማሪም አራት ትምህርት ቤቶች፣ አንድ ደረጃውን የጠበቀ ጤና ጣቢያ፣ አስራ ሁለት መካከለኛ ጥልቀት ያላቸው የመጠጥ ውሃ ጉድጓዶች እና አስራ ስድሰት አገልግሎት ሰጪ ተቋማት እንደሚገነቡ ከወልቃይት ስኳር ልማት ፕሮጀክት ጽ/ቤት የተገኘ መረጃ ያሳያል።

ልማቱ ከተጀመረ አንስቶ  የህዝብ ድጋፍ አልተለየውም። በተለያየ ጊዜ በተካሄዱ የምክክር መድረኮች የልማቱ አስፈላጊነት በህዝቡ ዘንድ በሰፊው ሰርጿል። በመሆኑም ህዝቡ  ልማቱን ለማፋጠን ከመንግሰት ጋር

ተባብሮ እየሰራ ይገኛል። ህዝቡ ልማቱ ከመሪ ድርጅቱ ህወሓት/ኢህአዴግ ጋር በመሆን ለረጅም አመታት ያደረገው ተጋድሎ ውጤት መሆኑን በሚገባ ተገንዝቧል።

አገሪቱ ድህነትን ታሪክ ለማድረግ የዘረጋችው የተቀናጀ ዘመቻ እውን ለማድረግ በከፍተኛ ደረጃ ያግዛሉ ተብሎ ከተያዙ የልማት እቅዶች  አንዱ የወልቃይት ስካር ልማት ፕሮጀክት መሆኑን በሚገባ የተገነዘበው የአካባቢው ህዝብ ለልማቱ መፋጠን ድርሻውን እየተወጣ ይገኛል።

እውነታው ይህ  ከሆነ  የዋልድባ ገዳምን አስታኮ እየተነሳ ያለው መሰረትየለሽ ጉዳይ መሰረቱ ምን እንደሆነ ለመገመት አያዳግትም።  ሃይማኖትን ለፖለቲካ አጀንዳ ማስፈጸሚያ መሳሪያ አድርጎ የመጠቀም አባዜ ነው።

ሃይማኖትን ለፖቲካ ተግባር ማዋል በአገራችንም ሆነ በሌሎች በርካታ የዓለማችን አገራት በተለያየ ጊዜ የተሰራበት ስልት ነው። አሁን ዋልድባ ገዳም ላይ እየተነሳ ያለው ጉዳይም ከዚሁ ፍላጎት የመነጨ እንጂ በገዳሙ የደረሰ ተጨባጭ ችግር ኖሮ አይደለም። የኢትዮጵያ ህዝብ ለሃይማኖቱ ቀናኢ መሆኑን የተገነዘቡ ግን  የኢትዮጵያ ልማትና ብልጽግናን ማየት የማይሹ አካላት የአገሪቱን ልማት ለማደናቀፍ እያቀነባበሩ የሚያቀርቡት ዘመቻ ነው።

ይሁን እንጂ  በልማቱ ላይ  ያነጣጠረ ማንኛውም ዘመቻ በወልቃይት ህዝብ ዘንድ ተቀባይነት የለውም። ህዝቡ በፈጠራና በሃሰት ፕሮፖጋንዳ  የማይወናበድ መሆኑን የአከባቢው ነዋሪዎች ይናገራሉ። አቶ ተጠምቀ ገ/መድን ይህንን አስመልክቶ ሲገልጹ ልማቱ የራሳችን፣ ተጠቃሚዎች እኛው መሆናችንን ያወቅነው አሁን ሳይሆን ገና ልማቱ ለመጀመር በታሰበበት ወቅት ባደረግነው ውይይት ነበር። ያኔ በልማቱ ጠቀሜታ ዙሪያ ከመንግስት አካላት ጋር ተከታታይ ውይይቶችን  ባደረግንበት ወቅት ነበር በሚገባ የተገነዘብነው ይላሉ።

የስኳር ልማቱ በቀጥታ ከሚሰጠን ጥቅም ባሻገር ከዚሁ ጋር ተያይዞ ከሚስፋፋው መሰረተ ልማትና ማሕበራዊ አገልግሎቶች ተጠቃሚዎች እንሆናለን ብለዋል።  እንደ ነዋሪዎቹ እምነት  በመስኖ፣ በዓሳ ምርትና በእንስሳት ማድለብ ተግባራት በመሳተፍ ኑሯቸውን ለማሻሻል ያስችላቸዋል። ስለሆነም የአካባቢው ነዋሪዎች ልማቱን በሙሉ ልብ ይደግፋሉ።

የአምስት ዓመቱ የእድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ በቀጣይ ሶስት ዓመታት በተጠናከረ መልክ በመተግበር አገራችንን ከድህነት በማላቀቅ መካከለኛ ገቢ ካላቸው አገራት ተርታ ለማሰለፍ የተጀመረው የተቀናጀ ዘመቻ እውን በማድረግ የወልቃይት ስኳር ልማትም የጎላ ድርሻ ይኖረዋል። ከዚህም ባሻገር የወልቃይት አካባቢ መሰረተ ልማት መሟላትና ሌሎች ተቋማት መገንባታቸው አካባቢውን ይቀይሩታል። የህዝብ አኗኗር ሙሉበሙሉ ይለወጣል፣ ይሻሻላል።

ይህ ማለት ግን ሥራው ተጠናቋል ማለት አይደለም። በቀጣይ ሶስት ዓመታት የተጀመረውን የልማት አቅጣጫ አጠናክሮ መቀጠል ያሻል። አጠቃላይ የአገሪቱ ልማት በተያዘለት የጊዜ ገደብ በማጠናቀቅ አገሪቱ

በድህነት ላይ ያወጀችውን የተቀናጀ ዘመቻ ዳር በምታደርስበት ወቅት የወልቃይት ህዝብም በአካባቢው የተጀመረው ልማት ተጠናቆ የላቀ ጠቀሜታ የሚያገኝበት ሁኔታ ይፈጠራል።

የሰሜኑ የአገራችን ክፍል ለበርካታ ዓመታት በድርቅ የተጎዳ ህዝብ ነው። ተፈጥሮ ያደለውን ጸጋ በሚገባ መጠቀም የሚያስችለው ዕድል ጠባብ ነበር። በተለይም ቅድመ 1983 የወልቃይትና አካባቢው ህዝብ ለከፍተኛ ርሃብ ስደትና ስቃይ ይዳረግ እንደነበር የቅርብ ጊዜ ታሪክ ነው። አሁን ላይ ሆነን በቀደሙት ስርዓታት የነበረውን የህዝቡ ሁኔታ ስንቃኝ በወቅቱ ኖረን አይተነው ካልሆነ በስተቀር ለማመን ያስቸግራል።

የአካባቢው ህዝብ የዕለት ጉርሱን ለመሸፈን ተቸግሮ ይሰደድ ከነበረበት ዘመን ወጥቶ አሁን ውሃ የማቆርና እርሻን የማልማት ስራ አጧጡፎታል። ከዚሁ ጎንለጎን ደግሞ ዘመናዊ የእንስሳት እርባታን በማስፋፋት ተጠቃሚ እየሆነ ይገኛል።

አሁን በአካባቢው እየተገነባ ያለው የስኳር ልማት ፕሮጀክት ሲጠናቀቅ ደግሞ የበለጠ ተጠቃሚ እንደሚሆን አውቋል። ለዚህም ነው ልማቱን ለማፋጠን ከመንግስት ጎን ተሰልፎ የበኩሉን ድርሻ እየተወጣ የሚገኘው። በድህነት ላይ ያነጣጠረው የተቀናጀ ዘመቻን እውን ለማድረግ ህዝብና መንግስት እጅና ጓንት ሆነው እየሰሩ ይገኛሉ፤ ዘመቻውም ያለምንም እንከን ይሳካል። በሌሎች አካባቢዎች እየተገነቡ ስላሉ አዳዲስ የስኳር ልማት ፕሮጀክቶችና የማስፋፊያ ስራዎች አጠቃላይ ሂደትና ያሉበትን ደረጃ በቀጣይ ክፍሎች እንዳስሳለን።